# የሞተ አመለካከት አብዮት አይለኩስም

ኢብሳ ነመራ 8/22/11

በቅርቡ የሐገሪቱን ሠላምና ፀጥታ በማደፍረስ ሕገመንግስታዊ ሥርዓቱን ለማፍረስ ተንቀሳቅሰዋል በሚል ወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ሥር ከዋሉት ግለሰቦች አንዱ የሆኑት አቶ እስክንድር ነጋ በቁጥጥር ሥር ከመዋላቸው ከሣምንት ቀደም ብሎ "ጥናታዊ ፅሁፍ" በሚል አንድ ፅሁፍ ማቅረባቸው ይታወሳል፡፡ "ትግሉ ወደ ሠላማዊ ተግባር ይሸጋገር" በተሰኘ ርዕስ፣

በቅድሚያ ይህ የአቶ እስክንድር ነጋ ፅሁፍ ፀሃፊው ጥናታዊ ይበሉት እንጂ፣ በመረጀ ላይ ያለተመሠረተ፣ ምናልባት ከአንድ የጋዜጣ መጣጥፍነት የማይዘል በስሜት የታጀለ የግል አስተያየት ነው፡፡ ታዲያ ይህ የግል አስተያየት "ላም እሣት ወልዳ …… " እንዲሉ በፀሐፊው የግል ዕምነትና በእውነታ መሃከል ተፋጦ፣ ወዲህ የግል ስሜትን በማንፀባረቅ፣ ወዲህ ደግሞ ዕውነትን በመፍራት ወዲያና ወዲህ እየረገጠ የቀረበበት ነው፡፡ በዚህ አኳኋን ተዘባርቆ/ተሳክሮ የቀረበው የፅሁፉ ይዘት ይህ ነው ብሎ መረዳት የሚያዳግት ቢሆንም፣ ጎልተው በወጡ አንዳንድ ሐሳቦች ላይ አስተያየት መስጠት አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።በጽሁፉ ላይ የቀረበውን ሃሳብ በራሣቸው መንገድ ተርጉመውት ሊምታታባቸው የሚችሉ፣ አለያም ውል አልባ የሆነው ፅሁፍ አላማ ምንነት አልያዝላቸው ያለ ዜጎች ሊኖሩ ስለሚችሉ፡፡

ከፅሁፉ ርዕስ እንጀምር። ርዕሱ "ትግሉ ወደ ሰላማዊ ተግባር ይሸጋገር" ይላል፡፡በቅድሚያ ይህ የፅሁፍ ርዕስ ለጥናታዊ ሥራ የሚሰጥ ሣይሆን መፈክር ነው። ምናልባት መፈክር ለመሆን ጎደለው የሚባል ነገር ቢኖር የቃለ አጋኖ ትዕምርተ ምልክት ብቻ ነው፡፡ ይህ በፅሁፉ አናት ላይ የሠፈረው መፈክር ይዘቱ ባይገባም አላማ ግን አለው፡፡ የተዘበራረቀውን ባለ7 ገፅ ፅሁፍ አንብቦ ለመጨረስ ትዕግስት ያላቸው ዓላማውን በፅሁፉ መደምደሚያ ላይ ሠፍሮ ያገኙታል፡፡ ይህም "በ2004 ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሟላ ዴሞክራሲ ሀገር እንድትሆን ሠላማዊና ሕጋዊ ትግል ከቃላት ወደ ተግባር የሚሸጋገርበት ይሁን፡፡ ከዚህ በኋላ

ቃላት ትርጉም የላቸውም፡፡ የሚባለው ሁሉ አልቋል፡፡ የቀረው ሠላማዊ ህጋዊ ትግል ነው፡፡ ተግባር ነው፡፡” የሊሚለው ጥሪ ነው፡፡ ከዚህ ዝቅ ብሎም ሌላ የመደምደሚያ መፈክር ሠፍሯል፤ “በሠላማዊና ሕጋዊ መንገድ ታሪክ ይሠራ” የሚል መፈክር፡፡

የፅሁፉ አናት ላይ የሠፈረው “ትግሉ ወደ ሠላማዊ ተግባር ይሸጋገር” የሚል መፈክር የተገለፀበትን ሀሣብ ይዘት እንመልከት፡፡ በ2004 ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሟላ ዴሞክራሲ ሀገር እንድትሆን "ሠላማዊና ሕጋዊ ትግል ከቃላት ወደ ተግባር ይሸጋገር" የሚለው ላይ ላዩን ሲያዩት፣ ራሣቸው አቶ እስክንድር ሃሳብን በነፃነት የመግልፅ መብት በህግ ከተረጋገጠበት ከ1984 ዓ\ም ጀምሮ በነፃ ጋዜጠኝነት ሽፋን ሲያራምዱት የነበረው ፅንፈኛ ጦር አውርድ የሚል ሠላማዊና ሕጋዊ ያልነበረን ትግል ትቻለሁ፣ ከሁን በኋላ ሠላማዊና ሕጋዊ መንገድ እከተላለሁ የሚል ቃል ኪዳን ይመስላል፡፡ “የሚባለው ሁሉ አልቋል፡፡ የቀረው ሠላማዊና ሕጋዊ ትግል ነው፡፡” በሚል ያስከተሉት  ደግሞ ይህንኑ መላ ምት የሚያረጋግጥ ይመስላል፡፡

ይሁን እንጂ፣ በፅሁፉ አንድም ቦታ ላይ ስለምርጫና በሕዝብ ድምፅ ስለሚገኝ የስልጣን ውክልና በጨረፍታ እንኳን ሳላልጠቀሱ ስለምን አይነት ሠላማዊ ትግል እንደሚያወሩ መገመት ያስቸግራል።ምክንያቱም አንድና ብቸኛው የሠላማዊ ትግል መገለጫ ምርጫና በሕዝብ ውክልና የሚገኝ የመንግስት ሥልጣን ርክክብ በመሆኑ ፡፡ እንግዲህ አቶ እስክንድር ወዲህ ሠላማዊ ትግል ብለውና በሌላም በኩል ምርጫ የሚለውን ጉዳይ ቃሉን እንኳን ለመጥቀስ አለመውደዳቸው “ሠላማዊ” የሚለውን ቃል ፣ሰላማዊ ያልህነ ስውር ዓላማቸውን ለመሸፈን የተጠቀሙበት መሆኑንና ሰላማዊ ያልሆነ የትግል ሥልት መፀነሳቸውን ያመላክታል፡፡ ከሠላማዊ ትግል ውጭ ያለው አማራጭ ደግሞ አንድም ፖለቲካውን አልቻልኩትም ብሎ አርፎ መቀመጥ፣ አለያም ሕጋዊና ሠላማዊ ያልሆነ ትግል መከተል ነው፡፡አቶ እስክንድር “አርፌ እቀመጣለሁ” የሚለውን አማራጭ ስለልመረጡ፣ የመረጡት ሕጋዊ ያልሆነ ትግልን ነው ማለት ነው፡፡

አሁን የመፈክርነት ይዘት ካለው በአቶ እስክንድር ከቀረበው የፅሁፍ ርዕስ ወጥተን ወደ ፅሁፉ ይዘት እንዝለቅ፡፡ የፅሁፉ መግቢያ ባለፉት 20 አመታት በአሜሪካ አራት ፕሬዚዳንቶች፣ በእንግሊዝ አራት ጠቅላይ ሚኒስትሮች፤በደቡብ አፍሪካ ሦስት መሪዎች መለዋወጣቸውን ያስታውሳል፡፡ ኢትዮጵያ ግን ይህን አይነት የመሪ መለዋወጥ አለመስተናገዷን ጠቅሶ፣ “ኢህአዴግ ደክሟል ሌላው ቢቀር ቢያንስ ከ20 አመት በኋላ እረፍት ያስፈልገዋል፡፡” ይላል፡፡

አቶ እስክንድር ይህን ሲሉ የመሪና የፓርቲ መለዋወጥ መኖሩን እንደ ዴሞክራሲያዊነት መገለጫ ከጠቀሱዋቸው ሦስት አገራት ውጭ፣ ፍፁም ዴሞክራሲያዊና ሠላማዊ የሆኑ ለ20 አመታት ብቻ ሳይሆን ከ20 አመታት በላይ እድሜ ያሥቆጠረና እሥካሁንም የዘለቀ፣ አንድ ፓርቲ በምርጫ እያሸነፈ በህዝብ ውክልና ስልጣን ላይ የቆየባቸው የዓለም አገራትን ለምን መጥቀስ አልደፈሩም። ጥናታዊ ፅሁፍ ሁሉን ያጣቀሰ አሣማኝ መከራከሪያ ሐሣብ የሚቀርብበት እንጂ፣ የግል ፍላጎትን ለማንፀባረቅ የዕውነት አንድ ጎን ተቦጭቆ የሚጠቀሥበት ባለመሆኑ፣ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ እንድትሆን የግድ የተለየ ፓርቲ ሥልጣን ላይ መውጣት ይኖርበት እንደነበር፣ በቀጣይነትም የግድ ሌላ ፓርቲ መመረጥ እንዳለበት የማረጋገጥ አቅም የለውም፡፡

እዚህ ላይ ዋናው መታየት ያለበት ነገር፣ የመንግስት ሥልጣን ብቸኛ ምንጭና ባለቤት የአገሪቱ ዜጐች መሆናቸው ነው፡፡ ሕዝብ በድምፁ የሥልጣን ውክልና እስከሰጠ ድረስ አንድ ፓርቲ ላልተወሰነ ጊዜ ሥልጣን ላይ መቆየቱ አማራጭ የሌለው አማራጭ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ አቶ እስክንድር መከራከር ካለባቸው ተጨባጭ ማስረጃዎችን እያቀረቡ ከዚህ ቀደም በአገሪቱ የተካሄዱት ምርጫዎች የሕዝብ ውክልና ያልታየባቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ ብቻ ነው፤ልብ በሉ በሥሜት ሳይሆን በተጨባጭ ማሥረጃ አሥደግፈው። በፅሁፋቸው ላይ አንድም ቦታ ይህን ማድረግ አልፈቀዱም ወይም አልደፈሩም፡፡

ፅሁፉ ከመግቢያው ቀጥሎ ባቀረበው ሃሳብ፣ ምናልባት መንደርደሪያ ሊባል ይችል ይሆናል@ “ስለ ጳጉሜን ወር፣ ስለ አስራሦስት ወር ፀጋ፣  በምን ሳይንሳዊ መስፈርት

ተመዝኖ እንደሆነ ሳይገለፅ ለፅሁፍና ለንባብ ምቹ የሆነ የራስዋ ፊደል ያላት መሆኑ (ኢትዮጵያ የራሷ ፊደል ባለቤት መሆኗ እንደበጎ ነገር የሚወሰድ መሆኑ ሳይዘነጋ)፣ ብቸኛዋ ጤፍ የሚበላባት አገር መሆኗን፣ በአጠቃላይ ኢትዮጵያ የቀደምት ሥልጣኔ አገር መሆኗን ያትታል፡፡ በማያያዝም "ኢትየጵያ በታሪኳ አንድም ጊዜ አንድ ቋንቋ የሚነገርበት አንድ ሐይማኖት የሚመለክባት አገር ሆና እንደማታውቅም ይነገራል፡፡

እርግጥ ነው ከላይ የተገለፁት ኢትዮጵያን ከሌላው ዓለም የሚለዩዋት መገለጫዎቹ መሆናቸው አይካድም። ነባሩ የኢትዮጵያ ሥልጣኔ በየራሳቸው መልከዐ ምድር የሚኖሩ ፣የየራሣቸው መገለጫ ያላቸው ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ውጤት መሆኑንም እንዲሁ። ኢትዮጵያ የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪ ብሔሮችና ብሔረሰቦች የሚኖሩባት፣ የተለያዩ ሐይማኖት ተከታዮች የሚኖሩባት አገር መሆኗንም እውነት ነው፡፡ እዚህ ላይ አቶ እስክንድር ያልጠቀሱትና ዋናው መታየት የነበረበት ጉዳይ ግን በቀድሞዎቹ አገዛዞች "የተለያዩ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ማንነታቸው ሕጋዊ ዕውቅና ተሰጥቶት፣ ብሔራዊ ማንነታቸው ተከብሮላቸው ነበር ወይ ሲኖሩ የቆዩት?" የሚለው ነው፡፡

እውነታው ዘውዳዊው ሥርዓት በመስፋፋት የያዛቸው አካባቢዎች የሚኖሩ በርካታ ሕዝብ ያላቸው ብሔሮችና ብሔረሰቦች ማንነታቸው የሕግ ዕውቅና ተነፍጎት፣ ዘውዳዊው መንግስት በፈለቀበት ብሔር ቋንቋና ባሕል እንዲኖሩ ጫና እየተደረገባቸው ይኖሩ የነበረ መሆኑ ነው፡፡ ሐይማኖትን በተመለከተም ሁኔታው ተመሣሣይ ነበር፡፡ ቁም ነገሩ የተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሐይማኖቶች በአንድ የፖለቲካ ወሰን ውስጥ መካተታቸው ሳይሆን መብትና ነፃነታቸው በትክክል መከበሩ ወይም አለመከበሩ ነው፡፡ አቶ እስክንድር በፅሁፋቸው ስለኢትየጵያ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሲጠቅሱ የመብትና የነፃነታቸውን ጉዳይ የማንሣት ወኔ ለምን አጡ? ስለነበረው ሁኔታ ስለማያውቁ? ማጣቀሻ መፅሐፍ ስላጡ? ወይንስ ልባቸው ዕውነታውን ስለማይፈቅደው ? መልሱን ለፀሓፊውና ሃሳባቸውን ለሚጋሯቸው እንተወው፡፡

በሥልጣኔና በመንግሥት ዙሪያ የሚያትተው የአቶ እስክንድር ፅሁፍ ክፍል፣ የኢትዮጵያ ዘውዳዊ የመንግሥት ሥርአት የሦስት ሺህና ከዚያም በላይ ዕድሜ ያለው መሆኑን ጠቅሶ፣ ይህም ኢትዮጵያ የሥልጣኔ አገር ብቻ ሳትሆን ሕዝብ የእኔ ነው የሚለው መንግስት የነበራት መሆኑኗን ያረጋግጣል፡፡  ኢትዮጵያ የረጅም ዘመን የጭቆና ታሪክም የላትም ብሎ ውዳሴ ዘውዳዊ መንግስት አቅርቧል፡፡

ይህ እንግዲህ የጸሐፊው ዕምነት መሆኑ ነው፡፡ እውነታው የሚያረጋግጠው ግን በኢትየጵያ የቆዩት ዘውዳዊ ሥርአቶች የነገሥታቱን፣ የመሣፍንቱንና መኳንንቱን ጥቅምና ፍላጎት ለማስጠበቅ፣ ሕዝብን እንደግል ንብረታቸው ፍላጎታቸውን ለማሥጠበቅ በሚያመቻቸው መንገድ ጨቁነው ሲገዙ መኖራቸውን ነው ፡፡ ነገስታቱ፣ መሣፍንቱና መኳንንቱ የአገሪቱን መሬት የግል ርሥታቸው አድርገው፣ ኑሮው በመሬትና በግብርና ላይ የተመሠረተውን ባለአገር መሬት አልባ አድርገው ዘርማንዘሩ ለዘመናት ሰፍሮ የኖረበትን መሬት በጢሠኝነት እያረሠ፣ ምርቱን ብቻ ሣይሆን ጉልበቱን ጭምር ሲገብር መኖሩ የቅርብ ግዜ ትውሥታችን ነው፡፡ አርሶ አደሩ ነገሥታቱና መሣፍንቱ  ግዛታቸውን ለማስፋፋት በሚያደርጉት ውጊያ ላይ እንዲሰለፍ እየተገደደ ህይወቱን ሲያጣ፣ በሌላ በኩል ያለችው  ንብረቱ በአሸናፊው ወገን  ሲዘረፍ፣ ሚስቶቹና ሴት ልጆቹ ሲደፈሩ መኖሩም እውነት ነው፡፡ አቶ እስክንድር የኢትዮጵያ “ሕዝብ የኔ ነው የሚለው መንግሥት የነበረበት፣ የረጅም ዘመን የጭቆና ታሪክ ያልነበረበት” ብለው ውዳሴያቸውን ያዥጎደጎዱት እንግዲህ ይህን ለመሰለው ዘውዳዊ ሥርዓት ባላቸው ታማኝነት ነው፡፡

አቶ እስክንድር ይህ  ስለዘውዳዊ ሥርአት ያላቸው ዕምነት አጠገባቸው ያሉትንና ከጎኔ ይሠለፋሉ ያሉትንም ሊያስኮርፍ የሚችል መሆኑን ገምተው ይመስላል ወይም ሊካድ የማይችል ሆኖ አምልጧቸውም ሊሆን ይችላል የተወገረገረ ማስመሠያም አቅርበዋል፡፡ በኢትየጽያ ያነበረው ዘውዳዊ ሥርዓት በህዝብ ተመርጦ የተሰየመ ይምስል፣ “በህዝብ ነፃ ፍላጎት የቆመ ነበር ፣ከአድዋ ጦርነት በኋላ ባሉት 100 አመታት ግን፣ አውሮፓውያን ሬኔሰንስ፣ ኢንላይትመንትና ሪፎርሜሽን ወይም የትንሣኤ፣ የብርሃንና የለውጥ ዘመን የሚሏቸው ወደ ኢትዮጵያ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጠቅለው ገብተው ዘውዳዊው ሥርዓት በሕዝብ ፍቃድ ከቆመ መንግስትነት

በሕዝብ ትከሻ ላይ በጉልበቱ ወደተፈናጠጠ አምባገነናዊ ሥርዓት ተቀይሯል፡፡ የ1966ቱ አብዮት የዚህ ውጤት ነው፡፡” በማለት ነው የተውገረገሩት፡፡ ልብ በሉ አሁንም ቢሆን ዘውዳዊው ሥርዓት ጨቋኝ ነበር አላሉም፡፡ ሕዝቡ ያልተቀበለው ስለተጨቆነ ነው ማለትም አልደፈሩም፡፡

በመቀጠል አቶ እስክንድር ጭቆና የወለደው ሊሉት ያልደፈሩትን፣ ከዚህ ይልቅ በአውሮፓ ተካሂዶ የነበረውን ሪፎርሜሽን የተቀበሉ ልሂቃን ውጤት እንደሆነ አስመስለው ያቀረቡልን የ1966 አብዩት መጨናገፉን፣ የ1983ቱ አብዮትም የዚህ ውጤት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ እዚህ ላይ አንድ እውነት ተናግረዋል፡፡ጭቆና የወለደው የ1966ቱ አብዮት፣ ለህዝቡ የመብትና ነጻነት ጥያቄ ምላሽ መሥጠት ያልቻለ በመሆኑ ተጨናግፏል፡፡ ከ1967 እስከ 1983 ማገባደጃ ለ17 አመታት ያህል ሥልጣን ላይ የነበረው የወታደራዊ ቡድን አምባገነን የመንግስት ሥርዓት ምን ሲያደርግ እንደነበረ ገና ከትውስታችን ያልጠፋ የቅርብ ገዜ ታሪካችን በመሆኑ ሃተታ ማቅረብ አሥፈላጊ አይመሥከለኝም፡፡በሁሉም የገሪቱ አቅጣጫ የትጥቅ ትግል ያካሄዱ በርካታ የነፃነት ግንባሮች የተፈጠሩትም ለዚህ ነው፡፡ በመጨረሻም የወታደራዊው ቡድን አምባገን ሥርዓት የፈረሰው እነዚህ የበርካቶችን የሕይወትና የአካል መስዋዕትነት በጠየቀ መራራ የትጥቅ ትግል መሆኑም ይታወቃል፡፡

አቶ እስክንድር ግን የ1983ቱም አብዮትም ተጨናግፏል ይሉናል፡፡ በዚህ ሳቢያም አሁን አገሪቱ ለውጥ ማርገዟንም አርድተውናል፡፡ ለለውጥ የሚያነሳሱ ቅድመ ሁኔታዎችም ማሟላታቸውንና የመንግሥት ለውጥ ለማምጣት ምርጫ መጠበቅ እንደማያስፈልግ ጭምር ፡፡ሥርዓቱን ለመጣል ተነሱ የሚል ጥሪ ያስተላለፉትም ከዚህ የግል እምነታቸው በመነሳት ነው፡፡

አሁን ለለውጥ የሚያነሳሱ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና፣ ኢኮኖሚያዊ ቅድመ ሁኔታ በሚል ያቀረቡዋቸውን ሃሳቦች እንመልከት፡፡ እንደፖለቲካ ቅድመ ሁኔታ ከቀረቡት እንጀምር፡፡

ፖለቲካዊ ቅድመ ሁኔታን አስመልክተው በሚያስገርም አኳኋን ከዚህ ቀደም የተለመዱትን የፖለቲካ ምህዳር ጠበበ፣ ምርጫው ተጭበርብሯል… ወዘተ የሚሉትን ጉዳዮች አላነሱም፡፡ በደፈናው ኢትዮጵያ አሁን ትልቋ የአምባገነኖች ሃገር ሆናለች ከሚል መደምደሚያ ነው የተነሱት፡፡ ትልቋ አምባገነን ለማለት ያበቃቸውን ምክንያት በማስረጃ ተንትነው አላስረዱም፡፡ በደፈናው እስከ ቅርብ ጊዜ ናይጀርያ በአንደኛ ደረጃ፣ ግብፅ በሁለተኛኛ ደረጃ እንደነበሩ፤ ናይጀርያ ከወራት በፊት ዴሞክራሲያዊ ምርጫ በማካሄዱ፣ በግብፅም በሕዝባዊ አመፅ ሥርዓቱ በመወገዱ፣ ሦስተኛ ሆና የቆየችው ኢትዮጵያ አንደኛ ሆነች ነው ያሉን፡፡

ከዚህ ውጭ ኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ አፈና መኖሩን ያሳያል በሚል እንደቀረበ መረጃ ሊጠቀስ የሚችል ነው በማለት አንድ ነገር አቅርበዋል፡፡ ይህም ተቃዋሚዎች "በ2001 ዓ.ም በፓርላማ ውስጥ የነበራቸው 178 መቀመጫዎች በ2002 ወደ አንድ መቀመጫ ዝቅ ብሏል" የሚለው ነው፡፡

እርግጥ ነው በናይጀርያ ከዚህ ቀደም ያልታየ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ተካሂዶ ይችል ይሆናል፡፡ ዋናው ነገር ኢትዮጵያ ውስጥ ከዚህ ቀደም ምርጫዎች መካሄዳቸው፣ በቀጣይም የሚካሄዱ መሆኑ ነው፡፡ይህ በማንም ቸርነት የተሰጠ ሳይሆን፣ በሕገመንግስት የተረጋገጠ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም የተካሄዱት ምርጫዎች የተሟሉና ዴሞክራሲያዊ አይደሉም ቢባል እንኳን፣ ከናይጄሪያው ልምድ አኳያ መነሳት የሚኖርበት ቀጣዩ ምርጫ የተሻለ ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን ምን መደረግ አለበት የሚለው ነው፡፡ አቶ እስክንድር በዚህ ዴሞክራሲያዊ፣ ሠላማዊና ሕጋዊ አካሄድ የሚያምኑ ቢሆን ኖሮ ማድረግ የሚጠበቅባቸው (ፓርቲ ይኑራቸው አይኑራቸው አላውቅም እንጂ)፣ ፓርቲያቸው አለያም የሚደግፉት ፓርቲ ካለም የሕዝብን ጥያቄና ፍላጎት ያገናዘበ አቋምና ፖሊሲ ኖሮት ወደህዝብ ዘልቆ እንዲንቀሳቀስ፤ደጋፊ እንዲያፈራ በመጨረሻም በህዝብ ድምፅ ሙሉ በሙሉ ወይም በአብላጫ ድምጽ አለያም በወሳኝ መጠን የምክር ቤት መቀመጫ አግኝቶ በሕጋዊና ሰላማዊ ውድድር ሥልጣን እንዲረከብ ወይም እንዲጋራ መስራት ነበር፡፡ ፓርቲ ከሌላቸውም በፈቀዱት አመለካከት አደራጅተው ወይም ሕጋዊ ሆነው

የሚንቀሳቀሱትን መቀላቀል፡፡ ይህንን ግን አልፈለጉትም፡፡ ከምርጫ የተሻለ ሠላማዊ የዴሞክራሲያዊ የፖለቲካዊ ትግል አማራጭ ያለ ይመስል፣ ምርጫን የማይመለከት "ሠላማዊ" ትግል መካሄድ አለበት የሚል ጥሪ ነው ያስተላለፉት፡፡ ይህ አካሄድ ሕገወጥ የኃይል እርምጃ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ሠላማዊ የምትለዋ ቃል ማደናገሪያ ነች፡፡በሕገ ወጥ መንገድ ዕልጣን ለመመንተፍ የሚደረግ እንቅሥቃሤ ደግሞ በህግ ያስጠይቃል፡፡

አቶ እስክንድር ሁለተኛዋ አምባገነን ነበረች ያሏትን ግብፅ የጠቀሱት የአመፅ ዓላማዬን ተገቢነት ያረጋግጥልኛል በሚል ነው፡፡ እርግጥ ግብፅ ውስጥ አምባገነን ሥርዓት ነበር፡፡ የሙባርክ መንግሥት በድጎማ ኢኮኖሚ ህዝቡ የፖለቲካ ጥያቄ እንዳያነሣ አፋቸውን ለጊዜው ሸብቦ የኖረ መንግሥት ነበር፡፡በህዝቡና በመንግስት መሃከል፣ መንግሥት ድጎማውን ያላማቋረጥ ሊሰጥ፣ ሕዝቡም ለዚህ የመንግስት ውለታ ተቃውሞ ላያነሳ ውስጠ ታዋቂና ያልታወጀ ወይም ያልተጻፈ የተዳፈነ "ስምምነት" ነበረ፡፡ይሁን እንጂ የሙባርክ ምንግስት በመጨረሻ ህዝቡ ከዚህ በኋላ ምንም አያመጣም ብሎ ንቆ ድጎማውን አስቀረ፡፡ የፕሬዚዳንት ሙባረክና የጓደኞቻቸው ልጆች፣ የኒዮሊበራሊዝም አመለካከት አራማጅ የሆኑ ጥቂት ቱጃሮችንና በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ ሲሠሩ የቆዩ ተመሣሣይ አመለካከት ያላቸው ጥቂት ግብፃውያንን ያካተተ ቡድን ሁኔታዎችን ማደላደል ይጀመራል፡፡ ቱጃሮችን ብቻ የሚመለከተው ኮረፖሬት ታክሥ በከፍተኛ መጠን እንዲቀነሥ፣ በተቃራኒው ቀደም ሲል ሲያገኘው የነበረው ድጎማ የቀረበት ዝቅተኛው የህብረተሰብ ክፍል የሚከፍለው ግብር እንዲጨምር ይደረጋል፡፡ በዚህ ሁኔታ የኑሮ ሁኔታው ከነበረውም የባሰ አሥከፊ ሆኖበት ተስፋው የጨለመበት የግብፅ ሕዝብ ሥርዓቱን በኃይል ለመገርሰስ እንዲነሳሳ ተገደደ፡፡ ሌላ አማራጭ አልነበረውማ፡፡

የኢትዮጵያ ሁኔታ ግን ፍጹም ከዚህ የተለየ ነው፡፡መንግስት ህዝቡን የሚያኖረው በድጎማ ሳይሆን፣ ወደ ታች ወርዶ የራሱን ሃብት መፍጠር እንዲችል የሞያና የገንዘብ(የብድር አገልግሎት) እንዲያገኝ ማድረግ ነው፡፡ የሚከተለው ፖሊሲ፣ አንድ ቀን ሊቋረጥ የሚችል ህዝብን በድጎማ የማኖር ስትራቴጂ ሳይሆን፣ ህዝብ የራሱን ሃብት እንዲፈጥር የሚያነሳሳ ልማታዊ ፖሊሲ ነው፡፡በገጠር የአርሶና አርብቶ

አደሩን፣ በከተማ ደግሞ የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞችን እንቅስቃሴ መመልከተ ለዚህ በቂ አስረጂ ነው፡፡ ይህ አብዛኛውን የኢትዮጵያ ህዝብ በልማት ፖሊሲው ተጠቃሚ የሆነው፣ተጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል የተረዳው አርሶና አርብቶ አደር እንዲሁም በአነሥተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ላይ የተሰማራው ከተሜ፣ መንግስት ሐብት እንዲያፈራ፣ የተሻለ ሕይወት እንዲኖር እያገዘው መሆኑን ይረዳል፡፡ ማንም በመሰረተ ቢሥ ጥላቻ የታወረ ግለሰብ ወይም ቡድን “ ጃሎ መገን” ብሎ ባቅራራ ቁጥር ለአመጽ የማይነሳውም ለዚህ ነው፡፡ ለበለጠ ልማትና ውጤት ብሎም ተጠቃሚነት እንጂ አቢዮት ሊቀሰቅስ የሚችል ነባራዊ ሁኔታ የለም ማለት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ በዘህ አኳኋን ከግብፅ የተለየ ቢሆንም አቶ እስክንድር በጥላቻ የተቃኘ የፖለቲካ ተቃውሞና የግል ፍላጐትና ጥቅም  የግብፅ አመፅ ወደ ኢትዮጵያ ይዛመታል ብለው  እንዲነመጁ አድርጓቸዋል፡፡ አብዮት እንደኮሌራ የሚተላለፍ፣ ወይም እንደአንበጣ በንፋስ የሚዛመት አለያም አንድ ጸሃፊ እንዳሉት እንደሸቀጥ ከውጭ የሚገዛ ሳይሆን፤ ነባራዊ ሁኔታ የሚፈጥረው በመሆኑ፣ ምኞታቸው ከቅዥትነትና ከማይሆን ምኞትነት አልፎ የትም እንደማይደርስ ማረጋገጫው ይህ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ከ20 ዓመት በፊት በርካታ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ማንነተቸው ለ100 አመታት ያህል  በሕግ ዕውቅና ተነፍጎት ይደርስባቸው የነበረው ፖለቲካዊና ማሕበራዊ ጭቆና  አክትሟል፡፡እንዲሁም ዘውዳዊውን ፊውዳላዊ ሥርዓት ለመውደቅ ያበቃው የአርሶ አደሩ የመሬት ባለመብትነት ጥያቄ በአዋጅ ምላሽ ተሰጥቶት የነበረ ቢሆንም፣ ሥርዓቱ ይከተለው የነበረው የኢኮኖሚ ፖሊሲ አርሶ አደሩን የምርቱ ባለቤትነት መብቱን በማሣጣት ይደርስ የነበረው ኢኮኖሚያዊ ጭቆና  አሁን ምላሽ አግኝቷል፡፡ ምንም እንኳ በመሰረታዊ ባህሪው የራሱ የሆነ መለያዎች ያሉት ቢሆንም በግብፅ፣ በቱኒዚያና በሊቢያ የተቀሰቀሰው ዓይነት ሕዝባዊ አመፅና አብዮት ከ20 ዓመት በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ በስኬት ተካሂዷል፡፡ ይህ አብዮት የአትዮጵያን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፖለቲካዊ

ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መብታቸውን ለይስሙላ አስከብርላችኋለሁ ያለ ሣይሆን በሕገመንግስት ያረጋገጠ ነው፡፡

ከዚህ በተረፈ በ2001 የተቃዋሚዎች የፓርላማ መቀመጫ 178 የነበረው በ2002 ወደ አንድ ዝቅ ማለቱን በመጥቀስ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ላይ አፈና መኖሩን ለማሣየት የተቀመጠውን በተመለከተ፣ ለዚህ ዋነኞቹ ተጠያቂዎችና ባለቤቶች ራሣቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች መሆናቸው ሊታወቅ ይገባል፡፡ እንደሚታወቀው በ1997 ዓ.ም በተካሄደው 3ኛ ዙር ምርጫ የቀድሞው ቅንጅት አዲስ አበባን ሙሉ በሙሉ ከማስተዳደር በተጨማሪ በፌዴራል የሕዝብ ተወካለች ምክር ቤት ከኢሕአዴግ ቀጥሎ ከፍተኛ ቁጥር ያለው መቀመጫ አግኝቶ እንነበር ይታወቃል፡፡በአጠቃላይ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከፍትኛ ቁጥር ያለው የፓርላማ መቀመጫ ተጋርተው ነበር፡፡ ይህ የአገሪቱ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መጎልበት ያስገኘው ውጤት መሆኑ ዕውነት ነው፡፡ ከተቃዋሚዎቹ በተለይ አቶ እስክንድርም በአባልነት የታቀፉበት የቀድሞው ቅንጅት ይህን ዴሞክራሲያዊ የሥልጣን ውክልና በገዛ ፍቃዱ ተወው፡፡ በኋላ ላይ ግን ዘግይተው ሁሉም ምናልባትም /ከሁለትና ሦስት የማይበልጡ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች በስተቀር/በእርግጠኝነት አብዛኞቹን የቆጫቸው እርምጃ እንደነበር ይታወቃል፡፡ የዚህ ፓርቲ አመራሮች ድምፅ የሰጣቸው ከፍተኛ ቁጥር ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአመፅና በነውጥ ሁሉንም መንግሥታዊ ሥልጣን ነጥቆ እንዲሰጣቸው ጠይቀው ነበር ውክልናውን አሻፈረኝ ያሉት፡፡ እንዳሰቡት ድምፅ የሰጣቸው ሕዝብ በሙሉ ዴሞክራሲያዊ ያልሆነውን የሥልጣን ነጠቃ ለማስፈፀም በአመፅ ሳይተባበራቸው ቀርቶ ለሥልጣን ምንተፋ የታሰበው አመፅ ከከተማ ሁከትነት ሣይዘል በሕጋዊ መንገድ በአጭሩ ተቀጭቷል፡፡ የአመፅ ጠንሣሾችና አስፈፃሚዎቹም በፍርድ ቤት ክስ ተመስርቶባቸው የፍርዱ ሂደት ቀጥሎ የቀረበባቸውን የጥፋተኝነት ማስረጃ መከላከል ሥላልቻሉ ቅጣት ተወስኖባቸው እንደነበር ይታወሳል፡፡ የሆነ ሆኖ የፍርድ ውሳኔውን ተከትሎ በነበሩት ጥቂት ወራት ውስጥ መንግሥትንና ሕዝብን በይፋ ይቅርታ ጠይቀው ከማረሚያ ቤት መውጣታቸውም ይታወቃል፡፡

ቅጣታቸው በይቅርታ ተነስቶ ከእስር ከወጡ በኋላ ሠላማዊ የፖለቲካ ተሣትፎ የማድረግ ሕገመንግስታዊ መብታቸው ተከብሮላቸዋል፡፡ እነዚህ የፓርቲ አመራሮች

ከሌሎቹ በቀድሞ ፓርቲያቸው ሲንቀሳቀሱ፣ የተቀሩት አዲስ ፓርቲ አደራጅተው በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ፡፡ እርግጥ አንዳንዶች ሰላማዊ ትግል፤የተወሰኑት ደግሞ በአጠቃላይ ፖለቲካዊ ተሳትፎ በቃኝ ብለው ባህር ማዶ የፈረጠጡም አሉ፡፡

ይሁን እንጂ የተወሰኑት ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ በሕዝብ ውክልና  ሥልጣን ለመረከብ ወደ ሕዝብ ዘልቀው የፖለቲካ ሥራ ከመሥራት ይልቅ፣ በዱላ እስከመከታከት በዘለቀ የእርስ በርስ ሽኩቻ ሲተራመሱ ነው የቆዩት፤ እስካሁንም ድረስ ትርምሳቸው አላባራም፡፡ የነዚህ ፓርቲዎች አመራሮች ፖለቲካን የግል ስሜታቸውን ለማስታመም ያህል እንደትርፍ ሰዓት ሥራ በመያዛቸው፣ በሌላ በኩል ደግሞ በእርስ በርስ ሽኩቻ በመጠመዳቸው የሕዝብን ቀልብ መግዛት አልቻሉም፡፡

ሁኔታቸውን የታዘበውና ያዘነባቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ደጋፊያቸው የነበሩ ጭምር "እንኳንም የመንግስት ሥልጣን ለመረከብ አልበቁ አገሪቱን ይበታትኗት ነበር፡፡" እያላቸው ነው፡፡ ይህን ከእነርሱ አንዱ የነበሩት ፐ/ር መስፍን ወልደማርያምም በግልፅ ተናግረውታል፡፡ ምርጫ 2002 ላይ የሕዝብ ድምፅ ያጡት የገሪቱ የፖለቲካ ምሕዳር ስለጠበበና ስለታፈኑ ሣይሆን፣ አንድም በቅንነት ምንም የፖለቲካ ሥራ ስላልሰሩ፣ ሌላም ሕዝብ ድርጊታቸውን አስተውሎ አይበጁም የሚል እምነት አድሮበት ስላልመረጣቸው ነው፡፡ ይህን እነርሱም ልባቸው ያውቀዋል፡፡ በሌላ በኩል ኢህአዴግ ቀደም ሲል ሲያደርገው ከነበረው የበለጠ የፖለቲካ ሥራ ሠርቶ ሕዝቡ ላይ እምነት እንዲያድር ማድረጉ ደግሞ ሽንፈታቸውን አብሶታል፡፡ እውነቱ ይህ ነው፡፡

አቶ እስክንድር ሌላ ለውጥ የግድ የሚል ነባራዊ ሁኔታ በሚል የጠቀሱት ነገር በ2001 ዓ.ም የፀደቀውን የሲቪል ማህበራትና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች አዋጅ ነው፡፡ይህን አዋጅ በተመለከተ በተደጋጋሚ አስተያየት ተሰጥቷል፡፡በአጭሩ አዋጁ አትዮጵያ ውስጥ የሲቪል ማህበራትና በጎ አድራጎት ድርጅቶች አይቋቋሙ አይልም፡፡ የሚለው ከ10 በመቶ በላይ በጀታቸውን ከውጭ አገር ምንጭ የሚያገኙ ማሕበራትና ድርጅቶች እንደ ውጭ አገር ድርጅት ይመዘገባሉ፤ የውጭ አገር ድርጅቶች ደግሞ በአገሪቱ የፖለቲካ ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ መግባት አይችሉም

ነው፡፡የውጭ አገር ድርጅቶች እንቅስቃሴ በልማት ሥራዎች የተወሰነ ነው፡፡ከዚህ በተረፈ የአገር ውስጥ ሲቪል ማህበራት ፖለቲካዊ ጉዳዮች ውስጥ ከመሳተፍ አልታገዱም፡፡

እነ አቶ እስክንድር የሚጠይቁት፣ የውጭ ሲቪል ማህበራት በአገራችንን የፖለቲካ ጉዳዮች እንዲፈተፍቱ እንዲፈቀድ ነው፡፡የቅርብና የሩቅ የዓለማችን ታሪክ የሚያሳየን ግን በውጭ ጣልቃ ገብነት የበለጸገ፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርአት የገነባ፣ ዘላቂ ሰላሙን ያረጋገጠ ሃገር አለመኖሩን ነው፡፡እነ አቶ እስክንድር የውጭ ማህበራቱ የአገራችንን ፖለቲካ እንዲያቦኩ የሚፈልጉት፣ አቧክተው ለዚህ ውለታ ከህዝብ ፍቃድ ውጭ ለሥልጣን የሚያበቃ ቀዳዳ እንዲምሱላቸው ነው፤ በቃ ፡፡

በአጠቃላይ አቶ እስክንድር በጽሁፋቸው ውዳሴ ዘውዳዊ ሥርአት ማቅረባቸው፣ የፖለቲካ እምነታቸውና አመለካከታቸው ከየት እንደተቀዳ ያመለክታል፡፡የተቃውሚቸው መነሻም ይህ የበሰበሰ አመለካከታቸው የፈጠረባቸው መሰረተ ቢስ ጥላቻ ነው፡፡ እናም አቶ እስክንድር የእርስዎ ዘውዳዊ አመለካከት አርጅቶ ሞቶ ወደ መቃብር እየወረደ እንጂ ተወልዶ እያደገ ባለመሆኑ፣ አብዮት ይቀሰቅሳል ብለው አይጠብቁ፡፡